# ትግላችን ዜና

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

P.O.Box 3198, 10364 Stockholm 3 SWEDEN

---

## የዴሞክራሲ መብቶች ረቂቅ አዋጅና አጭር

## መግቢያ

/በሚያዝያ ወር 1968 ዓ.ም ከብሔራዊ
ዴሞክራሲያዊ አብዮት ኘሮግራም ጋር
ሊታወጅ ተሰናድቶ የነበረ/

---

VOL. 5 No. 2 ቁጥር 2
November 1977 ጥቅምት 1970

## ለማስታወስ ያህል

"... 1/ ሕዝቡ በአብዮቱ መግፋት የሚችለው ነቅቶ፣ ተደራጅቶ፣ ታጥቆ ለትግሉ የተሟላ ዝግጅት ሲኖረው ብቻ በመሆኑና ይህ ዝግጅት የሰመረ ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ለመማር፣ ለማስተማር፣ ለመደራጀትና ለማደራጀት አስፈላጊ የሆኑት ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ ከሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ስለሆነ፣ ለፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ቢሮክራሲያዊ ቡርዧ፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በሙሉ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመደራጀትና የመሳሰሉት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በአስቸኳይ ከሥራ ላይ ማዋል::"

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም — ክፍል 3
ጊዜያዊ አጣዳፊ ተግባሮች::

"... 3ና የዴሞክራሲ ጥያቄ

በመደቦች በተከፋፈለ ማንኛውም ሕብረተሰብ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ዴሞክራሲ ላንዱ መደብ ነፃነት በሌላው መደብ ላይ ደግሞ ባርነትን የሚያጸድቅ ዴሞክራሲ እንጂ ለጠቅላላው ሕብረተሰብ እኩል ከሥራ ላይ የሚውል ዴሞክራሲ እንደሌለ ተደጋግሞ የተነገረ ሳይንሳዊ ሃቅ ነው:: ስለሆነም አብዮታዊያን የዴሞክራሲን ጥያቄ ከመደቦች ትግል ለይተው አይመለከቱትም:: የዴሞክራሲ መብቶችን የሚታገሉላቸው የተያያዙትን የነፃነት ትግሎች ለማፋፋም እንዲረዷቸው ስለሆነ እነዚህን መብቶች በትግል ይጎናጸፏቸዋል:: ለትግል መሣሪያ ያደርጓቸዋል:: የትግል መሣሪያ እንደመሆናቸው መጠን፣ ከመደቦች ትግል አንፃር እንደሚመለከቷቸው ሁሉ አብዮታዊያን የሚታገሉት ለጠላት መደቦች ለሚሆን ዴሞክራሲ ሳይሆን ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች ብቻ የሚውሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ነው::

በዚህ መሰረት ባሁኑ ወቅት አብዮቱን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉትን አድሃሪያን በይበልጥ ለመቋቋም በስውር ታፍነው የሚሠሩ ተራማጅ ድርጅቶች ትግላቸውን በይፋ ለማካሄድ እንዲችሉና በተለይ ደግሞ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ለመመሥረት የሚያስችሏቸውን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎችና ሰፋፊ ድርጅቶች ለማቋቋም እንዲችሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መታወጅ አለባቸው:: ለዚህም የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት የጋራ ትግል ያደርጋሉ::

... የጋራ መርሃ ግብር

... 2/ ይህንን የሰፊውን ሕዝብ መንቃትና በየፈርጁና በየደረጃው መደራጀት በማገዝ አስፈላጊ የሆኑት ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ እንዲለቀቁ በሕብረት መታገል:: "

የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች የጋራ መግለጫ::



"... ለዚህም የጓዶቻችንን ደም እጥፍ ድርብ አድርገን ለመበቀል የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች ለአድሃሪያን ፋታ ሳንሰጥ እናስታጥቃለን:: ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በይፋ እናረጋግጣለን::

የአገሪ ተገን የአብዮቱ አለኝታ የሆነው ሰፊ ሕዝብ በአብዮቱ ለሚያስፈልገው ሙሉ ተሳትፎ "ትጥቅና ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች" የሚለው መፈክር ከሥራ ላይ ይውላል::

... በመላ ኢትዮጵያ በሚሊዮን የሚቆጠረው ሰፊ ሕዝብ "ኢህአፓ፣ ኢድዩ፣ ኢኤልኤፍ አንድም ሶስትም ናቸው"፣ "ትጥቅ ለሰፊው ሕዝብ"፣ "ዴሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ ባስቸኳይ"፣ "አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሸጋገር" እያለ ያነገባቸው መፈክሮች የናንተ ብቻ ሳይሆኑ ዛሬ ከምን ጊዜውም ይበልጥ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትና የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች መፈክሮች ናቸው::"

የሊ/ቀ መንግሥቱ ኃይለ ማሪያም የአብዮት አደባባይ ንግግር
ጥር 27/1969 ::

"... ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ

ይህን ሁሉ ተመልክተህ ደጋግመህ በወተወተከው መሠረት ዛሬ አብዮትህ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ደረጃ ተሸጋገረ:: ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትና የኢትዮጵያ መለዮ ለባሾች ቋንቋቸው የሰፊው ሕዝብ ቋንቋ ነው:: እንዳንተው ኢህአፓና ኢኤልኤፍ ይውደሙ፣ የውስጥ አርበኞች ይውደሙ፣ ኢድዩና የውጪ አርበኞች ይውደሙ፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ሕዝብ ባስቸኳይ፣ ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ፣ አብዮታችን ከመከላከል ወደማጥቃት ደረጃ ይሸጋገር በለው በአንድ ድምጽ እንደቀደመው ከጎንህ ቆሟል::

... እንዳንተው አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሸጋገር ይላሉ እንዳንተው ኢህአፓ ኢድዩና ሲአይኤ ኢኤልኤፍ ይውደሙ ይላሉ፣ እንዳንተው ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ ይላሉ:: እንዳንተው ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ይላሉ፣ እንዳንተው አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት በለው ዛሬም ነገም ከጎንህ ይቆማሉ::"

በጥር 26/69 ከጊ/ወ/መንግሥት የተሰጠ መግለጫ::

## የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ ረቂቅ ይጸደቅ

በነሐሴ ወር 1969 ዓ.ም የመላ ኢትዮጵያ ሶሺያሊስት ንቅናቄ የትግል
ስልት በመለወጥ አንዳንድ ጓዶቹን ከህጋዊ የትግል መስክ ወደ ህቡዕ ማዛወሩ
የሚታወስ ነው::መኢሶን ይህ ርምጃ ለምን እንደ ተወሰደ ለማብራራት ባወጣው የሰ
ፊው ሕዝብ ድምጽ ቁ.61 ላይ የድርጅቱ አቋም አሁንም አብዮታዊ ሂስ መሆኑንና
የትግል ስልት የለወጠበት ዋናው ምክኒያት ይህንን አቋሙን ከማንም ተጽእኖና
ቁጥጥር ነፃ በሆነ ዘዴ በማራመድ ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የሚለተን የትግል
ዓላማ እሁም በግንባር ተደምነት ለማራመድ እንደሆነ አስረድቷል::ዐውነትም ከዚ
ያን ጊዜ ወዲህ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በንዑስ ከበርቴ ወላዋይነት የተነሳ
ሁኔታውን ከዕለትዕለት ለቀለበሳ እያመቻቸ መሄዱንና ራሱም ከአድሃሪያች ኩጥጥር
ስር መውደቁን እየተመለከተ እንደመኢሶን ነፃና ቆራጥ በሆነ መንገድ የጊዜያዊ
ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን በጦርነት ግርግር ሳቢያ ወደ ፀረ አብዮት እየዘፈቀ
መሄዱ አለማጋለጥ ታሪክ ምን ጊዜም ይቅር የማይለው አድርባይነት ነው::በፍርፋሪ
ተታሉ ወይንም ደግሞ ለጊዜው ኃያል በሚመስሉ አድሃሪያን ፊት ተርበድብደ በጊ
ዜው አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ አቋም አለመውሰድ ሰፊው ሕዝብ ራሱ ለሚያነሳቸው
አብዮታዊ መፈክሮች በግንባር ቀደምነት መታገል ትቶ እነሱን አፈር ለማለበስ
መሞከር፣ትላንት በ"ግንባር ቀደምነት" የተሰለፈባቸውን መፈክሮች ዛሬ ወርሶ
መካዱ የሚያመለክተው በኃያሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት መታሰፍን ወደታሪክ አተ
ላነት መወርወርን ብቻ ነው:: የመላ ሶሺያሊስት ንቅናቄ ትላንት ገራ መሰል አድ
ርባዮችን በቆራጥነት ተዋግቶ ከሰፊው ሕዝብ ጉያ እንዲተፉ አድርጓቸዋል::ዛሬ
ደግሞ ከመጀመሪያ አንስቶ እስካሁን ድረስ ከሰፊው ሕዝብ ጋር አብሮ ያነሳቸውን
መፈክሮች አንግቦ በግንባር ቀደምነት እየታገለ ነው::የቀኝ አድርባዮችና የታ
ሪክ አተላዎች የደርግን ታሪካዊ ሚና ውስንነት ስለማይረዱ፣በሰፊው ሕዝብ ቆራ
ጥነት እምነት ስለሌላቸው ዛሬ መኢሶን እነሱን ከክህደታቸው ጋር ወደኋላ ትቶ፣
ለአብዮቱ እንጂ ለሌላ ለማንም ኃይል ታማኝ እንዳይደለ በማስመስከር አሰፈቻው
ሲሄዱ ይህንን ድርጊቱን እንደ"መፈርጠጥ" ቆጥረውታል::እንደክህደት ቆጥረውታል::
መኢሶንም ሆነ በጠቅላላው የኢትዮጵያ አብዮታዊያን /በደርግ ውስጥ ያሉ አብዮ
ታዊያን ጭምር/ ምንጊዜም ታማኝነታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ ለደርግ እንደል
ሆነ ተደጋግሞ የተነገረ ነገር ነው::ዛሬ ደርግም ሆነ በሱ አካባቢ የተሰለፉ
የቀኝ አድርባዮች ትላንት የሚለተን የትግል ዓላማ ረስተው ሃገራችንንና አብ
ዮታችንን ለመከራና ለቀለበሳ እያመቻቹ እየተመለከተ ማንም አብዮታዊ፣ማንም አገር
ወዳድ ዝም የሚልበት ወቅት አይደለም:: የመኢሶን ጓዶች በዴፋ ስራ የተሰማሩት
የገራ መሰል ኢህአፓ አወናባጆች ይሉ እንደነበረት ለግላዊ የስልጣን ጉጉት አል
ነበረም::አሁን ደግሞ የቀኝ አድርባዮች የፈለጉትን ቢሉ የመኢሶን ጓዶች ህቡዕ
የገቡት "ለመፈርጠጥ" አይደለም::ከሃዲያንና አድርባዮች አፈር ለማለበስ የሚ-



ሞክሯቸውን የሰፊው ሕዝብ መፈክሮች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አንግበው በግንባር
ቀደምነት ለመታገልና ለመሰዋት ነው::

በመደብ ትግል ሃፍረት የሚሉ ነገር እንደሌለ ተደጋግሞ ተነግሯል::ስለ
ሆነም የኢትዮጵያን አብዮት እየከዱ፣ትላንት ከጣራ በላይ እየጮሁ ሲያስተጋቧቸው
የነበረትን መፈክሮች እንዳልነበረ እያደረጉ እየካዱ በኢትዮጵያ ሕዝብና በታሪክ
በመታለፍ ላይ ያሉት አተላዎች ዛሬ መኢሶንን "ተንሸራተተ" ፣ "አብዮቱ አለ
ፍት ሄደ" በማለት ያስተጋቡ ይዘዋል::ከአብዮቱ ትግል የተንሸራተተው ማነው?
የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄዎች ትላንት ተቀብሎ ዛሬ የካደው ማነው?እነዚህንስ ጥያ
ቄዎች አሁንም አንግቦ ወደፊት በመራመድ ላይ ያለው ማነው? መኢሶንና የተቀረት
የኢትዮጵያ አብዮታዊያን ናቸዉ ወይስ እነዚህን የሕዝብ ጥያቄዎች የሚቃወሙት
የቀኝ አድርባዮች?

እርግጥ መንሸራተት አለ::ግን በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከሰፊው ሕዝብ ትግል
ወደኋላ ተንሸራቶ አብዮቱን ለመግታት የሚፍጨረጨረው በአድሃሪያች እየተጥለቀለቀ
የሄደው ንዑስ ከበርቴው ደርግና በሱ አካባቢ የተሰለፉት ከሃዲያች እንጂ መኢ
ሶንና ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም::ይህንን ለመረዳት ዛሬ መኢሶን በግን
ባር ቀደምነት የተሰለፈለትን መላ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከዳር እስከዳር የሚ
ያስተጋባውን የዲሞክራሲ ጥያቄና ከሃዲያችና አድርባዮች በዚህ ጥያቄ ላይ እን
ዴት እንደተንሸራተቱ እንመልከት::

ራሱ ስሙ እንደሚያመለክተው የዲሞክራሲ ጥያቄ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ
አብዮት አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ነው::በመሬት ጥያቄ ላይ ከሚወሰደው አቋም እኩል
ይህም ጥያቄ የአብዮትና የፀረ አብዮት ኃይሎች መለኪያ ወሳኝ ጥያቄ ነው::
ለምን? ምክኒያቱም የመሬት ጥያቄ ራሱ ከሰፊው ሕዝብ ነፃነት ጥያቄ ጋር የተያ
ያዘ ነውና::ሰፊው ሕዝብ መሬቱን በአስተማማኝ ሁኔታ ከእጁ ሊያስገባና አጥብ
ቆ ሊገነባ የሚችለው ነፃነቱንም ተጎናጽፎ በቀደመው ሥርዐት የሥልጣን አውታ
ሮችና ቢሮክራሲ መቃብር ላይ የራሱን ሕዝባዊ አስተዳደር መገንባት ሲችል ብቻ
ስለሆነ ነው::ይህ በታላቅ ሌኒን ተደጋግሞ የተነገረ፣በብዙ አብዮቶች ታሪክ
የታዩና ከዚህ በፊት በሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥሮች ተደጋግሞ የተተቸበት ጉዳይ
በመሆኑ እዚህ ላይ አንመለሰበትም::በዛም ማተት ከማያስፈልግበት ምክኒያት አን
ዱና ዋናው የዛሬ ከሃዲያችና የቀኝ አድርባዮች ራሳቸው የዲሞክራሲን ጥያቄ እን
ደዋና ጥያቄ አድርገው እስከዛሬ አራትና አምስት ወር በፊት ይታገሉለት ስለነ
በር ነው::

እዚህ ላይ ስለዲሞክራሲ አስፈላጊነት ለመተቸት አልተነሳንም::ከአንድ
ዓመት በፊት በተለይ ይህንን ጥያቄ ለማወናበድ ተነስተው ከነበረት ገራ መሰል
አድርባዮች ጋር "ዲሞክራሲ ለምን ለማን" በሚለው ጥያቄ ላይ ሰፊ ክርክር ተካ

ሄደበታል።በዚያን ጊዜ መኢሶን ከገራ መሳይ አድርባዮች ጋር ባካሄደው የመረረ ትግል ዛሬ በዚህ ጥያቄ ላይ የአብዮቱ ሠፈር ከፍተኛ ጥራት አለው ማለት ይቻላል።

አድርባዮች፣ገራ መሳይ ይሁኑ የቀኝ አድርባዮች ዋና ምልክታቸው የሰፊው ሕዝብ ወገን መስለው ለማወናበድ የሚያሳዩት መቋመጥ ነው።ከንደዚህ አይነቱ አስመሳይ አቋማቸው ሊያናግላቸው የሚችለውና ወደታሪክ ትቢያነት የሚያዘውራቸው ዲሞክራሲ መሆኑን ያውቃሉ።ዲሞክራሲ እስከሌለ ድረስ በጨለማ ተሸፋፍነው ማወናበድ ይችላሉ።የዲሞክራሲ ብርሃን ካለ ግን አይሚያቸው አጥር ነው። የዛሬ የቀኝ አድርባዮችና የታሪክ አተላዎች ዲሞክራሲ ለኢህአፓ ምን ያህል አንዳሰበደው ተመለከተዋል።ስለዚህ ድርጅቱም ከአንገት በላይ ይቀበሉት የነበረውን የዲሞክራሲ ጥያቄ ዛሬ ገፍቶ ስለመጣባቸው ጨርሶ የሚክዱበት ደረጃ ደርሰዋል። ይህ ጉዳይ በተለይ ከንዑስ ከበርቴው መደብ ጥቅም አንፃር ሲታይ ራሱን የቻለ መደባዊ ምክንያት ስላለው ወደፊት ንዑስ ከበርቴውና የዲሞክራሲ ጥያቄ በሚል ርዕስ በሰፊው መመለስ ያስፈልጋል።የዛች አጥር ጸሐፊ ዓላማ ዛሬ ዓይን አውጥቶ መኢሶንና ሌሎች አብዮታዊያንን "ተንሸራተቱ" ብለው ለመከሰስ የሚሞክሩት የታሪክ አተላዎች የተንሸራተቱት ራሳቸው መሆናቸውን ለማስገንዘብና መኢሶን ትላንትም፣ዛሬም፣ነገም ምንግዜም ከሰፊው ሕዝብና ከጥያቄዎቹ ጋር በግንባር ቀደምነት የቆመና የሚቆም ድርጅት መሆኑን ባጭሩ ለመጠቆም ነው።ከዚህም ጋር አያይዘን ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ስምምነት ተደርስበት ነገር ግን ሳይታወጅ መሸገት የደመረውን "ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለሰፊው ሕዝብ ለማወቅ" የረቀቀውን አዋጅ አቅርበናል።ይህንን ማድረጋችን ዛሬ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ባስቸኳይ" እያሉ ከዳር እስከዳር የሚያስተጋቡት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ረቂቅ አካባቢ እንዲታገሉና ንዑስ ከበርቴው ደርግ መወላወሉን ትቶ ቃል የገባበትን አዋጅ ባስቸኳይ እንዲያውጅ ለማድረግ እንዲታገሉ ለማሳሰብ ነው።

ለመኢሶንና ለኢትዮጵያ አብዮታዊያን ሁሉ ይህ የዲሞክራሲ ጥያቄ ከመጀመሪያው አንስቶ የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ሆኖ ቆይቷል።እንዲያውም በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ላይ አብዮታዊያን የወሰዱት የ"አብዮታዊ ሂስ" አቋም አንዱ መስኩ ደርግ በየጊዜው የሚወስዳቸውን አብዮታዊ ርምጃዎች እየደገፈ ነገር ግን ደርግ እነዚህን ርምጃዎች ከሥራ ላይ ለማዋል እንደማይችል፣ከሥራ ላይ ሊያውላቸው የሚችለው ሰፊው ሕዝብ ብቻ መሆኑንና ለዚህም ብቁ ይሆን ዘንድ ሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ባስቸኳይ ታውቀውለት እንዲነቃ፣እንዲደራጅና እንዲታጠቅ መታገልም ነበር።

መኢሶን በተለይ በሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት አማካይነት ከጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ጋር ተባብሮ ለመስራት የወሰነው ደርግ በዚህ በዲ



ሞክራሲ ጥያቄ ላይ ተራማጅ የሆነ አቋም ለመውሰድ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አማካይነት በመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ቃል በመግባቱ ነው።

ዐውነትም በዚህ ፕሮግራም ላይ የፕሮግራሙ ዓላማ "የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያላንዳች ገደብ የሚከበሩበት፣ሕዝቡ በየደረጃው ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት...።" ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ለመመስረት እንደሆነ ተገልጧል።ግን ፕሮግራሙ ለንዑስ ከበርቴ ጨሌዎች ምንም መፈናፈኛ በማይሰጥ ሁኔታ የተነደፈ ነው። "ዲሞክራሲ የሚኖረው ሪፑብሊክ ስናቋቁም ነው።ፕሮግራሙ የሚለው እንዲህ ነው" ሊሉ አይችሉም።ምክንያቱም ፕሮግራሙ ከዚህ ዓላማ ለመድረስ ዲሞክራሲ ያስፈልጋል ብሎ እንዲያውም በምንም አይነት በማያሻማ አነጋገር ሰፊውን ሕዝብ ለማስተማር፣ለመደራጀትና ለማደራጀት አስፈላጊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች "ኅጧፊ" ናቸው ብሎ አስቀምጧቸዋል።በይዘታቸውም ላይ ምንም አይነት ወለምዘለም እንዳይኖር እነዚህ ዲሞክራሲያዊ መብቶች "ከንድ የወዘአደር ፓርቲ" ያውም ቢሮክራሲያዊ በሆነ ዘዴ ከላይ ለመወርወር ሳይሆን በጠቅላላው ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሆኑ ኃይሎች ሁሉ በየፈርጃቸውና በየደረጃው ማለትም በፓርቲዎች፣በልዩ ልዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች...ለመደራጀት የሚያስችላቸው መሆን እንዳለበት ዘርዝሯል።

መኢሶንና ሌሎች ሃቀኛ አብዮታዊያን ለዚህ ዓላማ ከዚያን ጊዜ ጀምረው ያለማወላወል ታግለዋል።በተለይ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አድሃሪዎች አጅግ አይለውበት ከመስከረም ወር 1969 ዓ.ም ጀምሮ ነጭ ሽብራቸውን ለመቋቋም ትጥቅና ዲሞክራሲ እያለ ሮሮ ሲያሰማበት በነበረበት ጊዜ መኢሶንና ዛሬም ከከዱት አንዳንዶቹ ለዚህ ጥያቄ በግንባር ቀደምነት ታግለዋል።ፀረ አብዮት ሲያይል ዲሞክራሲ መታፈኑ አይቀርምና እነዓላማየሁ ሃይሌ ይህንን የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄ ለማዳፈንና ለማፈን ተፍጨረጨሩ።ትጥቅና ዲሞክራሲ ተነፍጎ የሰፊው ሕዝብ ሰፈር አለቅጥ ተጠቃ።አብዮታችን ወደ ተከላካይነት ዘፈቀ።ቀለበስ አንዣበበ።አብዮታዊያን ከመቸውም ይበልጥ አብዮታችንን ሊያድን የሚችለው ኃይል ትጥቅና ዲሞክራሲ መሆኑን ተገንዝበው በቁርጥነት ታገሉ።ተራማጅ የደርግ አባላት ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም በአድሃሪዎች ላይ የማያወላውል ርምጃ በመውሰዳቸው አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋገረ።

እነዓላማየሁ ኃይሌ አፍነውት የነበረውን የትጥቅና የዲሞክራሲ መብት ጥያቄ በቁርጡ ከሥራ ላይ እንደሚውል ቃል ተገባ።በተገባውም ቃል መሠረት የተወሰነ ትጥቅ ያገኘው ሰፊ ሕዝብ መጠነኛም ቢሆን ዲሞክራሲያዊ መብቶችን እጅ አስገብቶ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁጥጥር ውጭ ነፃ ርምጃዎችን በመውሰድ በአድሃሪዎች ሰፈር ቀይ ሽብር እንዲነዛ አደረገ።ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ አጅግ በተደነቀ ዲሲፕሊን ራሱን በራሱ እየተቆጣጠረ በአድሃሪዎች ላይ ሽብር እየለቀቀ አብዮትን ወደፊት ሲያራምድ አድሃሪው ቢሮክራሲ ተገጨጨ፣ወላዋዩ ንዑስ ከበርቴ

ራሱም በሰፊው ሕዝብ ፊት ተርበደበዷልና የቢሮክራሲውን ውሸት ሰምቶ መሣሪያውን መንጠቅ ሲያቅተው ሰፊው ሕዝብ እጁ ያስገባቸውን ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንደገና ቀስ በቀስ እየፈለቀቀ ወደቢሮክራሲው መለሳቸው:: የቢሮክራሲው የበላይነት እንደገና ሰፈነ:: የሰፊው ሕዝብ መሣሪያ ለጊዜ የሚነገብ ነገር ብቻ ወደመሆን አዘነበለ:: ያለአድሃሪው ቢሮክራሲ ፈቃድ የአናርኪስቶቹ ዝንብ እሽ ማለት ተከለከለ:: ቢሮክራሲና ፀረ ዲሞክራሲ ተያይዘው በጭቁኑ ሕዝብ ላይ ነገሡ:: መንግሥት ራሱ በሰጣቸው ትጥቅ፤ሰፊው ሕዝብ መርጦ በሰጣቸው ህጋዊነት ተጠቅመው አድሃሪያንን መጣጠር ያቃታቸው ታጋዮች በቢሮክራሲው አሻጥር እንደገና ወደተከሳሽነት ተመለሱ:: መሰስ ተራማጆችን የሚያድነውና በተራማጆች ሠፈር ነጭ ሽበር የሚነዛው አድሃሪው ሠፈር ሆነ:: የዚህ ሁሉ ምንጭ በኛ ግምት እስከዚህም የትጥቅ መጥፋት ሳይሆን ሰፊው ሕዝብ በየካቲት ወር ተጎናጽፏቸው የነበረት ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ከእጁ ተፈራርቀው በመውጣታቸውና ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ከሰፊው ሕዝብ ሠፈር እየወጣ ከፀረ ሕዝቡ ቢሮክራሲ እየተሻረከ መሄዱ ነው:: ለዚህ ነው እንዲያውም ዛሬ አብዮትን እንደገና ወደአጥቂነት ለማሸጋገርና ከቀለበሳ ለማዳን ለዲሞክራሲና አድሃሪውን ቢሮክራሲ ለማውደም የሚደረገው ትግል ለአብዮታችን የሞት የሽረት ጥያቄ ሆኖ የሚገኘው:: ለዚህ ነው መኢሶን ዛሬ ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመቆም ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አንገብጋቢ ለሆኑት ለዲሞክራሲ መብቶች ዛሬም እንደትላንቱ ፀንቶ የሚቆመውና የሚዋጋው::

አድርባዮችስ? አድርባዮች ከዚህ ላይ ያላቸው ቦታ ያለ የአድርባይ መለኪያቸውን ነው:: የአድርባዮች አንዱ መለኪያቸው ሁሌ ጊዜ ከአየለው ጋር አይሉ መገኘት፤አብዮት ሲዳከም ከሰፊው ሕዝብ ሰፈር ከሁሉ ቀድመው መፈርጠጥ፤አብዮቱ ሲያይል ደግሞ ከሁሉ ይበልጥ የሰፊው ሕዝብ ወገን መስሎ "ከግንባር ቀደም ነት" መቆም ነው:: የዲሞክራሲ መብቶችን ጉዳይ አድርባዮች እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ወለ ምዘለም እያሉ ቢሆን ሲደገፉ ቆይተው ነበር:: የዲሞክራሲያዊ መብቶችን አጣዳፊነት ጉዳይ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ሲቀበሉ የተቀበሉ መስለው ነበር:: እንዲያውም አብዮቱ በርግጥ በአጥቂነት ደረጃ በነበረበትና በርግጥ መጠነኛም ቢሆን ሰፊው ሕዝብ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ነፃ በሆነ መንገድ ርምጃዎችን ይወስድበት በነበረበት ወቅት በአጭሩ መጠነኛ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን እጁ አስገብቶ በነበረበት ወቅት እነዚህ አድርባዮች "የተፈራረሙት" የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ሕብረት መርሃ ግብር ምን ይላል? አንዱ ነጥቡ በማንዣበብ ላይ ያለውን ፀረ አብዮት ለመደምሰስ አሁን ታፍነው የሚሠሩት ድርጅቶች በይፋ ሕዝቡን እንዲቀሰቅሱና እንዲያደራጁ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ እንዲታወጁ መታገል ያስፈልጋል ብለው ነበር:: ይህ እንግዲህ በየካቲት ወር መሆኑ ነው:: ሰፊው ሕዝብ አጥቂ በነበረበት ወቅት አድርባዮቹም "ከግንባር ቀደም ነት" መስለው ያሉት ነበር::

ከዚህ በኋላ መኢሶንና ሌሎች አብዮታዊያን ዛሬ የከፉት የማሌሪዩ ጊዜ



ቸም ጭምር ለዚህ መርሃ ግብር ታማኝ በመሆን "ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ" የሚለውን መፈክር አስተጋቡ:: ቀስበቀስ ቢሮክራሲ እንደገና እያንሰራራ፤አብዮቱ ተመልሶ ወደተከላካይነት እየዘፈቀና ቀለበሳ መልሶ ማንዣበብ በነበረበትና /አሁንም ባለበት/ ሁኔታ በዚህ ጥያቄ ላይ ያለው አብዮታዊ አቋም ይኸው ብቻ ነበር ፣ነውናም:: ይህንን መፈክር የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከአብዮታዊያን ጋር አስተጋባ:: ይህንንም ያደረገው መኢሶን ወይም ሌሎች አብዮታዊያን ስላነሱት አይደለም:: ከዐለታዊ ትግሉና ችግሮቹ ተነስቶ፤በየዐለቱ ፊውደፋሽስት ቢሮክራሲ የሚፈጽምበትን አሻጥርና ግፍ ተመልክቶ አብዮትን መልሶ ወደ አጥቂነት ለማሸጋገር ያለው አንድ መንገድ ይኸው ብቻ በመሆኑ ነው::

ነገር ግን የካቲት ላይ ግንባር ቀደም ይመስሉ የነበረት አድርባዮች ዛሬ የአብዮቱ በፈር ሲዳከም፤ሰፊው ሕዝብ ሲጠቃ ሲመለከቱ በአድሃሪያን ፊት ተርበደበው ለአድሃሪው ቢሮክራሲና ለፀረ አብዮት ማጎብደድ ጀመሩ:: በጠምላ ላይ በወጣው የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች የግብር ይወጣ የድርጊት ፕሮግራም ላይ የካቲት ላይ በአስቸኳይ ያስፈልጋል እንታገላለት፤እንሞትለት ይበለት የነበረው የዲሞክራሲ ጉዳይ እንዳልነበረ ሆኖ ተረሳ:: በጥቂት ሰዎች ድምፅ በለጫ የሚሊዮን ሰፊ ሕዝብ ጥያቄ "ዛሬ ዲሞክራሲ በቂ አለ:: ዲሞክራሲ አያስፈልግም" ተብሎ አፈር እንዲለብስ ተደረገ:: መኢሶን በሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁ.60 አጽንቶመለከተው ለሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች፤ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና ለየካቲቱ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች መርሃ ግብር ተከራክሮ በድምጽ በለጫ "ተሸነፈ":: በዚህ ሁኔታ ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አብይ በሆነው በዲሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ ከመንሸራተትም አልፎ ክህደት የፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለውን ወገን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል::

አድርባዮቹ የካቲት ላይ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ባስቸኳይ ያስፈልጋሉ ሲሉ ለዚህ የሰጡት ምክንያት "አብዮትን ለመቀልበስ ያሰፈሰፉ" ብዙ ኃይሎች ስላሉ በሀቡዕ "ታፍነው" የሚሠሩ ድርጅቶች ይፋ ወጥተው በተሉ ሕዝቡን ማደራጀት እንዲችሉ የሚል ምክንያት ነበር:: ዛሬ "ዲሞክራሲያዊ መብቶች አያስፈልጉም" ብለው ደፍረው ሲከራከሩ ለዚህ መንሸራተታቸውና ክህደታቸው የሰጡት አጥጋቢ ምክንያት የለም:: ነገር ግን በምንም አይነት የካቲት ላይ አብዮትን ለመቀልበስ "አሰፍስፈው" የነበረት ኃሎች ዛሬ ተደምስሰዋልና ዲሞክራሲ አያስፈልግም ብለው በሬ ወለደ ሊያሳምኑን አይችሉም:: በውጭና በውስጥ ከየካቲት 66 ዓ.ም ጀምሮ እስከዛሬም ፀረ አብዮት "አሰፍስፎ" እንደዛሬም ቀለበሳ በሩቻንን አንኳኩቶ አያውቅምና ወይም ደግሞ ዛሬ መርሃ ግብሩ ከወጣበት ከየካቲት 1969 ዓ.ም የተሻለ ከዚያ የበለጠ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ሰፍኗልም ብለው ሌላ በሬ ወለደ ሊያሳምኑን አይችሉም:: የዲሞክራሲን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ መመንመን፤የአድሃሪውን ቢሮክራሲ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ መንገሥ፤የሕዝባዊ ድርጅቶችን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ መዳከም፤የቀበሌ መሪዎችን፤የወዛደር መሪዎችን፤ሌሎች አገር ወዳዶችን

ከመቸውም ጊዜ በቀጥር ነፍሰገዳዮች እንደቀጠለ መርገፍ በአጭሩ የአብዮታችንን ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ወደተከላካይነት ዘፍቆ መምጣት እያየ ዛሬ በየካቲት 69 ይበልጥ ዲሞክራሲ አለ ማለት በአድርባይነት ታወር ወይም ለጊዜው ባየለው ነገር ግን ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና ከኃያሉ የኢትዮጵያ አብዮት ፊት ዘላቂነት በሌለው እምነት በቢሮክራሲ ተርበድብዶ የሃገሪቱን ቁጢጥ ሁኔታ መሳት ነው::ማንኛውም በሆነ ዛሬ የኢትዮጵያ ተራማጆች ክንድ እስከ ክንድ እጅ ለእጅ ተያይዘው በዚህ አንገብጋቢ ጥያቄ ላይ በአንድነት እንዳይተናነቁ መዘገበር የሚነዛ የአብዮትን ሰፈር ይበልጥ የሚያዳክም፣ቀለበሱን የሚያገዝ በታሪክ ፊት ይቅርታ የማይደረግለት ክህደት ነው ብለን እናምናለን::

ማህበራችን ከጠቅላላው ከኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብና በተለይ ከኢትዮጵያ ወጣቶች ጐን በመቆም ዛሬ ከምንጊዜውም ይበልጥ አንገብጋቢ ለሆነው ለፀረ ቢሮክራሲ ትግልና ለዲሞክራሲያዊ መብቶች እስከመጨረሻው ይታገላል::በዚህ ጥያቄ ላይ በመጽናት ያለአንዳች ማወላወል ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና ለየካቲት 69 ዓ.ም የማርክሲስት ሌኒኒስቶች ወርሃ ግብር ከሙሉ በመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ጋር አብሮ ይሰለፋል::ከሰፊው ሕዝብ ትግል የተገሸሩ ተቀትገና ታሰፊው ከሄዱ በኋላ ትግሉን ወደኋላ ለመጎተት የሚፍጨረጨሩትን የቀኝ አድርባዮች ያለርህራሄ ያጋልጣል::

ከዚች አጭር መግቢያ ጋር በሚያዚያ ወር 1968 ዓ.ም ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ሊታወጅ ተሰናድቶ የነበረውን የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ አያይዘን ለአንባቢያን አቅርበናል::ይህ ረቂቅ ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና በሱም ውስጥ ቃል ለተገባላቸው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲተናነቁ ያለፉት ጓደኞቻችን የሞቱለት ዓዋጅ ነው::የነሱን አርማ አንስቶ ትግላቸውን መቀጠል ማለት ዛሬ ይህ ረቂቅ ባስቸኳይ እንዲታወጅና አብዮቱ እንደገና ወደ አጥቂነት እንዲሸጋገር መታገል ማለት ነው::

የኢትዮጵያ አብዮታዊያን አርሶአደሮች፣ወዛአደሮች፣መለዮ ለባሾች፣ወጣቶች፣ሴቶች፣የጭቁን ብሄረሰብ ታጋዮች፣አገር ወዳድ ምሁራንና መካከለኞች የቀኝ አድርባዮችን ተንኮሎቻቸውን እያጋለጡ ለዚህ ዓዋጅ እንዲታገሉ አብዮታዊ ጥሪያችንን እናቀርብላቸዋለን::

የዲሞክራሲያዊ መብቶች አዋጅ ረቂቅ ይጽደቅ !
ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ይሁኑ !
ከመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ጋር አሁንም ወደፊት !
አስመሳዮችና አድርባዮች የታሪክ አተላዎች ናቸው !
ፊውዳሊዝም፣ኢምፔሪያሊዝም፣ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ይውደሙ !
የነቃ፣የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ አመጽ ያሸንፋል !





ረቂቅ

## ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በሥራ ላይ ለማዋል

## የወጣ አዋጅ:-

" ኢትዮጵያ ትቅደም "

1. የሰፊው ሕዝብ መንቃትና መደራጀት፣

ሀ/ ብሔራዊው ዲሞክራሲያዊ አብዮት በማያደርጥና በማያገግም ሁኔታ ወደፊት ለመራመድ ዋስትና የሚሆን በመሆኑ፣

ለ/ ለፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም መደምሰስ ማረጋገጫ በመሆኑ፣

ሐ/ ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች በወዛ-አደሩ የፖለቲካ ፓርቲ ግንባር ቀደምትነት አብዮታዊ የአንድነት ግንባር የሚመሠርቱበትን ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፣

መ/ ከዚህም የመነጨ ፀኑ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚቋቋምበትን ትክክለኛ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፣

ሠ/ የኅብረተሰብአዊነት /ሶሻሊዝም/ ርዕዮተ-ዓለም የሚስፋፋበትንና የሚዳብርበትን እንዲሁም ሶሻሊስት ኅብረተሰብ የሚመሠረትና የሚገነባበትን ጥርጊያ መንገድ የሚከፍት በመሆኑ፣

ረ/ የአገሪቱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጠላቶች ከሃቀኛ ደጋፊዎቻቸው ተለይተው እየተጋለጡ የሚገለሉበትን ወይም የሚመቱበትን ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፣

ሰ/ በየአቅጣጫው ምርት የሚያድግበትን፣ ንግድና ስርጭት የሚስፋፋበትን፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ድርጅቶች በተሻለ መልክ ለሕዝቡ ድርሻቸውን የሚያበረክቱበትን፣ በጠቅላላው የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቋም የሚሻሻልበትን ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፤

2. ሰፊው ሕዝብ ሊነቃ ሊደራጅ የሚችለው የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ለመማር፣ ለማስተማር፣ ለመደራጀት፣ ለማደራጀት እንዲሁም ሀሳባቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ለመግለጽና ለማሰማት ሲችሉ በመሆኑ፤

3. ይህን የመሰለውን ትግል ለማካሄድ አመቺ ሁኔታ ሊኖር የሚችለው ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሲታወጁና በትክክል ሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ በመሆኑ፤

4. ለፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች በሙሉ የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነቶች ታውጀዋል ::

## አንቀጽ ፩

**አጭር አርእስት፣**

ይህ አዋጅ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከሥራ ላይ ለማዋል በ1968 ዓ.ም. የወጣ አዋጅ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## አንቀጽ ፪

**ትርጉም፣**

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ሆኖ ካልተገኘ በቀር፣

1. “ዴሞክራሲ” ማለት ሰፊው ሕዝብ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በሶሻል ጉዳዮች ላይ በሙሉ ነፃነት በማተና ፍላጎቱን የሚገልጽበት፣ ጥቅሙን የሚያስከብር በት፣ የአብዮቱን መሥመር በጠራ ሁኔታ የሚቀይስበት፣ ራሱን በራሱ የሚያስ ተዳድርበት፣ የራሱን ዕድል በራሱ የሚወስንበት፣ በመቀሰሰው ድምፁን የሚያ ሰማበት፣ ሀሳቡን የሚገልፅበትና በመንግሥታዊ ውሳኔዎቹም ሆነ መዋቅሮች ላይ ተሳትፎውን የሚያረጋግጥበት ሕዝባዊ መብትና ሥርዓት ማለት ነው ። ሕዝባዊ ዴሞክራሲ ከፊውዳላዊ ዴሞክራሲና ከቡርዥ ካፒታሊስት ዴሞክራሲ ዓይነተኛ ልዩ ነት አለው ። ፊውዳላዊ ዴሞክራሲ በፊውዳል ሥርዓተ–ማህበር ውስጥ ሊኖር የሚችል ዴሞክራሲ ሲሆን፣ ያቀፈው መብትና ነፃነት የሚከበረውና በሥራ የሚ ተረጐመው ለፊውዳሎቹ፣ ማለትም ለመሬት ከበርቴ፣ የገዥ መደብ ብቻ ነው ። ብዙሃኑ ጭቁኑ ሰፊ ሕዝብ ከነፃነቱ አይጋራም ። የቡርዥ ካፒታሊስት ዴሞ ክራሲም ከዚሁ በብዙ አይለይም ። የሚለየው ነገር ቢኖር፣ የገዥው መደብ እንደመቀየሩ መጠን ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ የሚከበሩትና በሥራ ላይ የሚውሉት ለመሬት ከበርቴዎች ሳይሆን፣ ለአዲሱ የገዥ መደብ ለቡርዥ ካፒታሊስቶች መሆኑ ነው ። የመብቶቹ መኖር ሰፊውን ጭቁን ሕዝብ ገፋ ቢል ያወናብዱት እንደሆነ እንጂ፣ በተጨባጭ ሁኔታ ከቶ አይደርሱትም ። ሕዝባዊ ዴሞክራሲ ግን የአብዮቱ ባለቤት ለሆነው ለብዙሃኑ፣ በቀድሞው ሥርዓት ሲጨቆንና ሲረ ገጥ ለኖረው ሠርቶ–አደሩ ሕዝብና ለወገኖቹ በሙሉ በተጨባጭ ሁኔታ የሚረጋ ገጥለት መብት ነው ።

2. “ሰፊው ሕዝብ” ማለት የወዝ–አደሩ መደብ፣ የገበሬው መደብ፣ የንዑስ ከበር ቴው መደብና ሌሎች ፀረ–ፊውዳል፣ ፀረ–ኢምፔሪያሊስትና ፀረ–ቢሮክራሲያዊ ቡርዥ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች ማለት ነው ።

3. “ፊውዳሊዝም” ማለት በማንኛውም ኅብረተሰብ ታሪክ ውስጥ በአንድ በተወ ሰነ የታሪክ ዘመን ውስጥ ሰፍኖ የሚገኝ የሶሻልና የኢኮኖሚ ሥርዓት ወይም ስልተ–ምርት ነው ። ፊውዳሊዝምን ዓይነተኛ የሚያደርጉት ጠባዮች በሁለት



መልክ ሊታዩ ይችላሉ ። በምርት ኃይሎች በኩል መሬትና ዋና [illegible] መደብ [illegible] ሲሆን፣ በምርት ግንኙነቶች በኩል ደግሞ በበዝባዡ [illegible] ከበርቴው መደብና በተበዝባዡ የገበሬው መደብ መካከል ያለው ግንኙነት [illegible] መልክ ነው ። ሌላው የፊውዳል ስልተ–ምርት ልዩ ጠባይ ምርቱ ዓላማው [illegible] ነው ። ምርት [illegible] ለገበያ [illegible] ዓይነት የምርት ሥርዓት [illegible] ምርት [illegible] ሊባል ይችላል ።

4. “ኢምፔሪያሊዝም” ማለት ሞኖፖሊዎች የበላይነት የተቀዳጁበትና የፋይናንስ ካፒታሊዝም እራሱን ያደላደለበት ወቅት፣ ካፒታል ወደውጭ መላኩ ትልቅ ግምት የታየበት ወቅት፣ በዓለም አቀፍ የካፒታሊስት ድርጅቶች መካከል ዓለምን መከ ፋፈል የተጀመረበትና ታላላቅ የካፒታሊስት ኃይሎች ዓለምን ተከፋፍለው ያበ ቁበት የካፒታሊዝም የዕድገት ደረጃ ማለት ነው ።

5. “ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም” ማለት ከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት በሆኑና በኢምፔሪያሊስቶች የቅኝ አገዛዝ ወይም የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሥር በሚ ገኙ አገሮች ወይም ኅብረተሰቦች ውስጥ የሚገኘው የሶሻልና የኢኮኖሚ ሥር ዓት ማለት ነው ። ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ዓይነተኛ የሚያደርገው ጠባይ ከላይ ከተጠቀሰው ሌላ ከሥልጣን ላይ ሆኖ የመንግሥትን ቢሮክራሲ የሚመራ ቢሮክራሲያዊ ቡርዥ ተብሎ የሚጠራ የቡርዧ መደብ ክፍል መኖር ነው ። ይህ መደብ የአገር ውስጥና /መሬት ከበርቴውና የቡርዧው መደቦች/ የውጭ /ኢም ፔሪያሊስቶች/ በዝባዦች የፖለቲካ ወኪል ነው ። ከዚህም ሌላ አብዛኛው የመ ደቡ አባሎች ትምህርት ያገኙት በኢምፔሪያሊዝም ጥላ ሥር በኢምፔሪያሊስት አገሮች ውስጥ በመሆኑ በአስተሳሰባቸው፣ በባሕሪያቸው፣ በየቀኑ ኑሮአቸው ወዘተ...ከኢም ፔሪያሊስት ቡርዥ ጋር በቅርብ የተሳሰሩ ናቸው ።

6. “ፀረ–ፊውዳል” ማለት የመሬት ከበርቴው መደብ በልዩ ልዩ ማዕረጎች በመ ጠቀም በመደምሰስ ላይ የሚገኘውን የፊውዳል ሥርዓተ–ማኅበር ተመልሶ እንዲ ያንሰራራ ለማድረግና መንግሥታዊ ሥልጣንም እንደገና ጨብጦ ሰፊውን አርሶ– አደር ለመበዝበዝና ለመጨቆን የሚያደርገውን ትግል በጽናትና በአንድ የሚ ቃረን ማለት ነው ።

7. “ፀረ–ኢምፔሪያሊስት” ማለት ኢትዮጵያ በውጭ ኃይሎች የሚደረግባትን ማን ኛውንም የኢኮኖሚ ብዝበዛ፣ የፖለቲካና የሶሻል ተፅዕኖ እንዲሁም የባሕል ወረራ በጽናትና በአንድ የሚቃረንና ሌሎች አገሮች፣ ሕዝቦችና ብሔራዊ ኃይ ሎች ከቅኝ አገዛዝ፣ ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ፣ ከዘረኛነት፣ ፋሺስታዊ አገ ዛዝ ነፃ ለመውጣት የሚያደርጉትን ትግልና ወገንነ በተግባር የሚደግፍ ማለት ነው ።

8. “ፀረ–ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት” ማለት ኢምፔሪያሊዝምንና ፊውዳሊዝምን እንደ ሰንሰለት ሆኖ የሚያገናኘውን በከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት አገሮች ውስጥ

የሚገኘውን የቢሮ ቡርዧና በመሣሪያነት የሚገለገልበትን መንግሥታቸው ሁኔለሳ ድርጅታዊ መዋቅር በድርጊቱ በአቋም የሚፃረር ማለት ነው ።

9. “ ነፃነት ” ማለት ማንኛውም የሰፊው ሕዝብ ወገን ከፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት መሥመር እስካልወጣ ድረስ በልዩ ልዩ መልክና በተለያዩ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ዘዴዎች በመጠቀም ለመደራጀት፣ ለማደራጀት፣ በግልም ሆነ በጋራ ሀሳቡን ለመግለጽ ወይም ለማሰራጨት፣ ቅሬታውንም ሆነ ተቃውሞውን ለማሰማት፣ ድጋፍንና ስምምነትን ለመስጠት ወይም በሌላ መንገድ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ብሶቱን እንዲናገረው ለማድረግ በሕግ ተረጋግጦ የሚታወቅለት መብት ማለት ነው ።

10. “ የፖለቲካ ፓርቲ ” ማለት የአንድን መደብ ጥቅም መሠረት በማድረግ፣ በተዘረዘረ የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ በመመርኮዝ መንግሥታዊ ሥልጣንን ለመያዝ የሚታገል ድርጅት ማለት ነው ።

11. “ የፖለቲካ ድርጅት ” ማለት ለተወሰነ የፖለቲካ ግብ ወይም ዓላማ ለመታገል በመተባበር የተሰለፉ የሕዝብ ክፍሎች የአንድነት ግንባር ወይም ሌላ ንቅናቄ ማለት ነው ።

12. “ ሕዝባዊ ድርጅት ” ማለት በሙያ ወይም በሥራ መስክ ወይም በባሕል ግንኙነትም ሁነ፣ ተመሳሳይ አቋም የሚቀራረቡ ወይም የሚዛመዱ የሕዝብ ክፍሎች ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከባሕል ወይም ከሌላ የወል ጥቅማቸው ጋር የተያያዘ ዘውን ፍላጎታቸውን የሚያራምዱበትና የሚያስከብሩበት ድርጅት ማለት ነው ።

13. “ መደራጀት ” ማለት በፖለቲካ ፓርቲ መስክ፣ ወይም በፖለቲካ ድርጅት መስክ ወይም በሕዝባዊ ድርጅት መስክ በአንድ ተቋም ውስጥ በመተባበር ወይም በመጠቃለል ለፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግል መሰለፍ ማለት ነው ።

14. “ ንግግር ” ማለት ለአንድ ወይም ከአንድ ለሚበዙ፣ ቁጥራቸው ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ሰዎች ስለፖለቲካ፣ ስለኢኮኖሚ፣ ስለባሕል ወይም ስለማናቸውም ሌላ ጉዳዮች በቤትም ውስጥ ሆነ ከቤት ውጭ፣ በሕዝባዊ ሥፍራም ሆነ በግላዊ ሥፍራ፣ በቀጥታ በቃል ወይም በዘዋዋሪ በሬዲዮና በቴሌቪዥን አስተያየትን መግለፅ፣ መስበክ፣ ትምህርት መስጠት፣ የቅስቀሳ ተግባር ማከናወን፣ መተቸት፣ ወይም በሌላ ዓይነት ዘዴ ሀሳብን በቃል መግለፅ ማለት ነው ።

15. “ ጽሑፍ ” ማለት ስለፖለቲካ፣ ስለኢኮኖሚ፣ ስለባሕል ወይም ስለማናቸውም ሌላ ጉዳይ በደብዳቤ፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በመጽሐፍ፣ በፓምፍሌትም ሆነ በበራሪ ወረቀት፣ በተያትር፣ በፊልም፣ በዘፈንም ሆነ፣ በመዝሙር፣ በመፈክር፣



በግጥምም ሆነ በስድ ንባብ፣ በሥዕል፣ በቅርጽና በሌላ ሀሳብን የሚገልጹ ዘዴ ሀሳብን መግለጽ ማለት ነው ።

16. “ መሰብሰብ ” ማለት በሕዝባዊም ሆነ በግላዊ ሥፍራ የጦር መሣሪያ ሳይዙ ሀሳብ ለመግለፅ፣ ለመለዋወጥ፣ ወይም በማንኛውም ሌላ ዓይነት መንገድ ፍላጎትን ለመግለፅ መገናኘት ማለት ነው ።

17. “ ሰላማዊ ሰልፍ ” ማለት በሕዝባዊ ሥፍራ በመተላለፍ ወይም በመሰብሰብ መሣሪያ ሳይይዙ የሚመራና ድጋፍን ለመስጠት፣ ተቃውሞን ለማሰማት፣ ጥያቄዎችን ለማቅረብ፣ ሀሳብን ለመግለፅ፣ ደስታንም ሆነ ቅሬታን ለማሰማት የሚደረግ የሕዝብ ሰልፍ ማለት ነው ።

18. “ ሰው ” ማለት እንደአገባቡ በሰብአዊ ፍጡር ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም ድርጅት ማለት ነው ።

19. “ ድርጅት ” ማለት የፖለቲካ ፓርቲ፣ ወይም የፖለቲካ ድርጅት፣ ወይም ሕዝባዊ ድርጅት ወይም ሠሰተንም የሚያጠቃልል የወል ስም ነው ።

20. “ ሕዝባዊ ሥፍራ ” ማለት ማናቸውም አውራ ጎዳና፣ አደባባይ፣ መንገድ፣ ሜዳ፣ ድልድይ፣ የሕዝብ መናፈሻ ሥፍራ፣ ወይም የአትክልት ቦታ ማለት ነው ።

21. “ ግላዊ ሥፍራ ” ማለት ማናቸውም ንብረትነቱ የግለሰብ የሆነ ቤት፣ አዳራሽ፣ አጥር ግቢ፣ ወይም ሌላ ቦታ ማለት ነው ።

22. “ ጽሕፈት ቤት ” ማለት ጊዜያዊ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ማለት ነው ።

23. “ ተጠሪው ባለሥልጣን ” እና “ መዝጋቢው ባለሥልጣን ” ማለት ከዚህ በታች በአንቀጽ 7 ፣ 8 ፣ እና 12 የተመለከቱትን ተግባሮች እንዲያከናውኑ ጽሕፈት ቤቱ የሚመድባቸው ሰዎች ወይም ኮሚቴዎች ናቸው ።

## ክፍል 3

### የንግግር ነፃነት፣

1. ማንም ሰው ሙሉ የንግግር ነፃነት አለው ።
2. ማንኛውም ግለሰብ በዚህ ነፃነት በሚጠቀምበት ጊዜ የንግግሩ ይዘት ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት እስከሆነ ድረስ ማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ባለሥልጣን በቀጥታም ሆነ በዘዋዋሪ በኃይል

በመጠቀም ወይም ሥልጣንን መከታ በማድረግ ተፅዕኖ፣ ቁጥጥር፣ ምርምር፣ ክትትል በማድረግ ወይም በሌላ የአንገዳና የማስፈራሪያ ዘዴ በመጠቀም ሊከለክለው፣ ሊያስቸግረው ወይም ሊያውከው አይችልም ።

አንቀጽ 4

የጽሑፍ ነፃነት፣

1. ማንም ሰው ስለፖለቲካ፣ ስለኢኮኖሚ፣ ስለባህልና ስለማናቸውም ሌላ ጉዳይ ሀሳቡን በጽሑፍ ለመግለፅ ሙሉ ነፃነት አለው ።
2. ማንም ሰው በጽሑፍ ለመግለጽ የሚሻው ሀሳብ በይዘቱ ፀረ—ፊውዳል፣ ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ—ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግሉን የሚፃረር፣ ስለዚህም ፀረ—አብዮታዊ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ወይም የሌላውን ሰውም ሆነ በጠቅላላው የሕዝቡን መብት፣ ሕጋዊ ጥቅም፣ ሰላምና ሞራል የሚነካ ሆኖ ከተገኘ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ወይም መንግሥታዊም ሆነ የግሉ ወይም የድርጅታዊ ጋዜጣና መጽሔት አዘጋጆች ወይም አሳታሚዎች ሊከለክሉት ይችላሉ ።
3. ማንኛውም በታወቀ መንግሥታዊም ሆነ ግላዊ ወይም ድርጅታዊ ጋዜጣ፣ ወይም መጽሔት ወይም ደግሞ ታትሞ በወጣ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረው ጽሑፍ ፀረ—ፊውዳል፣ ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ—ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግሉን የሚጻረር በለዚህም ፀረ—አብዮታዊ፣ ወይም ደግሞ በጠቅላላው በሕዝብ መብት፣ ሕጋዊ ጥቅም፣ ሰላምና ሞራል ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ፣ በተቆጣጣሪው ባለሥልጣን አሳሳቢነት በጽሑፉ ደራሲና ጽሑፉን በኃላፊነቱ ባሳተመው ወይም ባሰራጨው ሰው ወይም ድርጅት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል ።
4. ማንኛውም በታወቀ መንግሥታዊም ሆነ ግላዊ ወይም ድርጅታዊ ጋዜጣ ወይም መጽሔት ወይም ደግሞ ታትሞ በወጣ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረው ጽሑፍ በግለሰብ መብትና ሕጋዊ ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ፣ ተገቢው በሚለው አመለካችነት የጽሑፉ ደራሲና ጽሑፉን በኃላፊነት ያሳተመው ወይም ያሰራጨው ሰው ወይም ድርጅት በፍርድ ቤት በሕጉ መሠረት ሊጠየቁበትና ፍርድ ቤቱም የአቤቱ ባዩን ጉዳት አረጋግጦ ካመነበት መልስ የመስጠት ወይም ማስተባበያ የማቅረብ መብትን ሊያስከበርለት ይችላል ።
5. አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ታትሞ በወጣ ጽሑፍ ሳቢያ ከፍተኛ ቁሳቁሳዊ ጉዳት የደረሰበት ከሆነና ጽሑፉ ሃሰተኛ የተሳሳተ መረጃ ላይ የተመሠረተ መሆኑን በፍርድ ቤት በማያሻማ ሁኔታ ካረጋገጠ፣ ፍርድ ቤቱ ለደረሰበት ጉዳት ተመጣጣኝ ካሣ ከጽሑፉ ደራሲ፣ አቅራቢና አሳታሚ እንዲከፈለው ለማድረግ ይችላል ።



አንቀጽ 5

የመሰብሰብ ነፃነት፣

1. የሰፊው ሕዝብ ወገኖች የመሰብሰብ ሙሉ ነፃነት አላቸው ።
2. የስብሰባው ዓላማና ይዘት ፀረ—ፊውዳል፣ ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ—ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግሉን የሚፃረርና በዚህም ፀረ—አብዮታዊ መሆኑ ከተደረሰበት፣ ወይም የሰፊውን ሕዝብ መብት፣ ጥቅም ሰላም፣ ወይም ሞራል የሚነካ መሆኑ በታወቀ ሊከለከል ወይም እንዲበተን ሊደረግ ይቻላል ።

አንቀጽ 6

ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት፣

ማንኛውም የሰፊው ሕዝብ ክፍል እንዲሁም ማንኛውም ድርጅት ለብቻውም ሆነ ከሌላ ድርጅት ወይም ድርጅቶች ጋር በመተባበር ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት አለው ።

አንቀጽ 7

ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ፈቃድ አስፈላጊ ስለመሆኑ፣

ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ከተቆጣጣሪው ባለሥልጣን አስፈላጊው ፈቃድ እንዲሰጥ ያስፈልጋል ።

አንቀጽ 8

ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ፈቃድ ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ፣

1. ማንኛውም ሰላማዊ ሰልፍ ከመደረጉ በፊት ቢያንስ አሥር ቀን አስቀድሞ የሰልፍ ፈቃድ መጠይቅ በሁለት ቅጅ በተዘጋጀ ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው ባለሥልጣን መቅረብ ይኖርበታል ።
2. ሰላማዊው ሰልፍ በአስቸኳይ ካልተደረገ ውጤቱ—ቢስ የሚሆን ከሆነ ወይም ሊያስተላልፈው የሚሻው መልዕክት በበርቱ የሚበረዝ ከሆነ፣ ሰልፉ ከመደረጉ በፊት ሦስት ቀን ብቻ አስቀድሞ ማመልከቻውን ማስገባት ይቻላል ።
3. የሚቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፣

ሀ/ ሰልፉን የሚያዘጋጀው ድርጅት ስምና አድራሻ፣

ለ/ ስለሰልፉ ዓላማ አጭር መግለጫ፣

ሐ/ ሰልፉ የሚደረግበትና የሚፈጸምበት ሁኔታ፣

መ/ ከሰልፉ በፊት ሕዝቡ የሚሰበሰብበት ቀን፣ ጊዜና ሥፍራ፣

ሠ/ ሰልፉ የሚያልፍባቸው መንገዶች፣ ጎዳናዎች፣ አደባባዮች፣ እንዲሁም የሚበተንበት ቦታ፣

ረ/ ሰልፉ የሚቆይበት ጊዜ በሰዓት፣

ሰ/ ከሰልፉ ጊዜ የሚያዙት መፈክሮች፣

ሸ/ በአስቸኳይ መደረግ ያለበት ሰልፍ ከሆነ አስቸኳይነቱን የሚያበስር መግለጫ፤

አንቀጽ ፱

የሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ አሰጣጥ፣

1. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ከዚህ በላይ በአንቀጽ 8 የተመለከተው ተሟልቶ ሲቀርብ፣ ማመልከቻውን በተቀበለ በሰባት ቀን ውስጥ የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል፤ ወይም መከልከሉን በጽሑፍ ለአመልካቹ ያስታውቃል ።

2. ለአስቸኳይ ሰላማዊ ሰልፍ ማመልከቻ በሁለት ቀን ውስጥ በተረፈ ግን ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው ሁኔታ መልሱን ያስታውቃል ።

3. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ የሚጠይቅ ማመልከቻ በተቀበለ በሰባት ቀን ወይም አስቸኳይ ጥያቄ ሲሆን በሁለት ቀን ውስጥ የተጠየቀውን ፈቃድ ያልሰጠ ወይም መከልከሉን በጽሑፍ ያላስታወቀ እንደሆነ ፈቃዱ እንደተሰጠ ተቆጥሮ በማመልከቻው ዝርዝር በቀረበው ሁኔታ መሠረት ሰልፉን ማድረግ ይቻላል ።

4. ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን የተጠየቀው ሰላማዊ ሰልፍ የፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግሉን የሚፃረር ስለዚህም የሰፊውን ሕዝብ አብዮት ለመፃረር የታሰበ ለመሆኑ ጠቢቅ ማስረጃ ካገኘ ወይም ሰልፉ የታቀደው ንብረት ወይም ሰው ላይ አደጋ ለማድረስ መሆኑን ካረጋገጠ፣ ምክንያቶቹን በጽሑፍ ለአመልካቹ ድርጅት፣ ለሰፊው ሕዝብ ደግሞ በይፋ ዝርዝር ገልጾ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል ።

5. ፈቃዱ በአግባቡ ያገኘ ሰላማዊ ሰልፍ በመካሄዱ ላይ ባለበት ጊዜ ይዘቱ ተቀይሮ ፀረ-አብዮታዊ መልክ የያዘ እንደሆነ ወይም በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ የቃጣ እንደሆነ፣ ወይም በማመልከቻው ካሰፈራቸው ሁኔታዎች ውጭ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን የፈጸመ እንደሆነ ሰልፉ በሰላም አስከባሪ ኃይሎች ሊበተን ይችላል ።



አንቀጽ ፲

የመደራጀትና የማደራጀት ነፃነት፣

የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሁሉ ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ትግሉን እስካልተፃረሩና ስለዚህም ፀረ-አብዮታዊ መሥመር እስካልተከተሉ ድረስ የመደራጀትና የማደራጀት ሙሉ ነፃነት አላቸው ።

አንቀጽ ፲፩

የፖለቲካ ድርጅት ስለመመሥረት፣

1. ማንኛውም ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት የሆነ የሰፊው ሕዝብ ወገን የፖለቲካ ድርጅት የመመሥረት ነፃነት አለው ።

2. የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ፕሮግራም ቢያንስ የኢትዮጵያ አብዮት መለስተኛ ፕሮግራምን የሚደግፍ የሚያከብር፣ የሚያራምድ ወይም የሚያሟላ መሆን አለበት።

3. የሚከተሉት ግለሰቦችና ክፍሎች ለመመሥረት፣ ወይም በመሪነትም ሆነ በአባልነት ለመሳተፍ፤ የፖለቲካ ድርጅቶችም ከነሱ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር የገንዘብም ሆነ ሌላ ዓይነት ዕርዳታና ድጋፍ ለማግኘት አይችሉም።

ሀ/ የፊውዳሉ ሥርዓት ምሰሶና ዐውቅ ተጠቃሚ የነበሩ፦ ለምሳሌ፣ ንጉሣውያን ቤተሰብ፣ መሣፍንቶች፣ መኳንንቶች፣ የመሬት ከበርቴዎች፣ ከፍተኛ የሃይማኖት ሹማምንቶች፣ ወዘተ...፤

ለ/ በቀደመው መንግሥት /ከየካቲት ወር 1966 ዓ.ም. በፊት/ ሚኒስትር፣ አምባሳደር፣ ጄኔራል ወይም የፖለቲካ ተሿሚ የነበሩና ከለውጡ ወዲህ የአብዮቱ ደጋፊ መሆናቸውን በሥራቸው ያላስመሰከሩ፤

ሐ/ ከምፕራዶር ወይም አቀባባይ ቡርዧዎች፦ ለምሳሌ፣ በውጭ አገር ካፒታል የተቋቋሙ የብዝበዛ ድርጅቶች ውስጥ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ፤

መ/ ከአሥር ሄክታር /ሩብ ጋሻ/ በላይ የገጠር መሬት የነበራቸውና የተወረሰባቸው፣ እንዲሁም የከተማ ቦታ ከ500 ካሬ ሜትር በላይና ትርፍ ቤት ከ$100.00 /አንድ መቶ ብር/ በላይ የሚከራይ የተወረሰባቸው ።

አንቀጽ ፲፪

የፖለቲካ ድርጅት ለመመሥረት ምዝገባ ስለማስፈለጉ፣

1. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት የድርጅቱን ደንብና ፕሮግራም አቅርቦ ካልተመዘገበ በቀር በፖለቲካ ድርጅትነት ታውቆ ሊሠራ አይችልም ።

2. የፖለቲካ ፓርቲ ለማቋቋም የሚፈልጉ ቡድኖች የሚከተሉትን መረጃዎች ለመዝጋቢው ባለሥልጣን ማቅረብ አለባቸው፤

ሀ/ የፓርቲውን ስምና አርማ፣

ለ/ የፓርቲውን ፕሮግራም፣

ሐ/ የፓርቲውን የመተዳደሪያ የገቢ ምንጭ፣

መ/ የፓርቲውን የመተዳደሪያ ደንብ፣

ሠ/ የፓርቲውን አድራሻ፣

ረ/ የፓርቲውን ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች ስምና አጭር የሕይወት ታሪክ፣

ሰ/ ፓርቲው የሚያወጣቸው ጋዜጦች ስሞች::

3. መዝጋቢው ባለሥልጣን ፓርቲ ለማደራጀት የሚጠይቅ ማመልከቻ በተቀበለ በሠላሳ ቀን ውስጥ የተጠየቀውን ፈቃድ ይሰጣል ወይም ይከለክላል ::

4. መዝጋቢው ባለሥልጣን የመመዝገቢያ ማመልከቻ በተቀበለ በሠላሳ ቀን ውስጥ አስፈላጊውን ፈቃድ ያልሰጠ ወይም መከልከሉን ከነምክንያቶቹ በጽሑፍ ያልገለጸ እንደሆነ ፈቃዱ እንደተሰጠ ይቆጠራል ::

አንቀጽ 13

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሕግ ሰውነት ስለመስጠታቸው፣

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በአንቀጽ 12 መሠረት የምዝገባውን ሥነ-ሥርዓት ካጠናቀቀ ወዲያውኑ የሕግ ሰውነት ይኖረዋል ::

አንቀጽ 14

የፖለቲካ ፓርቲዎች ስለሚኖራቸው ነፃነቶች፣

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በአንቀጽ 12 መሠረት የምዝገባውን ሥነ-ሥርዓት ካጠናቀቀ፣ ዓላማውን በይፋ ለማራመድ በዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች ሁሉ የመጠቀም ሙሉ መብት አለው ::

2. ልዩ ልዩ እንደወጣቶች ንቅናቄ፣ የሴቶች ንቅናቄ፣ የጥናት ክበብ የመሳሰሉትን ንዑስ ድርጅቶች በስሩ የማቋቋም መብት አለው ::

አንቀጽ 15

የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሕዝባዊ ድርጅቶች፣

1. የሰፊው ሕዝብ ወገኖች የፖለቲካ ድርጅቶችንም ሆነ ሕዝባዊ ድርጅቶችን የማቋቋም ነፃነት አላቸው ::



2. እነዚሁ ድርጅቶች በዓላማቸውም ሆነ በይዘታቸው ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት የሆነውን ትግል የሚደግፉ ወይም የማያደናቅፉ መሆን አለባቸው ::

3. በአቋማቸውም ሆነ በተግባራቸው አብዮቱን በኃይልም ሆነ በስውር የሚያሰናክሉ ሆነው ከተገኙ ሊታገዱ ይችላሉ ::

አንቀጽ 16

የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሕዝባዊ ድርጅቶች በምዝገባ አገባብ፣

1. የፖለቲካ ድርጅቶች በአንቀጽ 12 ስለፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባ ጉዳይ በተዘረዘረው ሁኔታ በተመሳሳይ መልክ መመዝገብ አለባቸው ::

2. ሕዝባዊ ድርጅቶች አቋማቸውና ዓላማቸው ፖለቲካ ነክ ከሆነ በአንቀጽ 12 በተዘረዘረው መሠረት መመዝገብ አለባቸው :: አቋማቸውና ዓላማቸው ፖለቲካ ጠቀስ ካልሆነ ግን በአገር አስተዳደር ሚኒስቴር በኩል ተራ ምዝገባ ብቻ ይጠየቅባቸዋል ::

አንቀጽ 17

የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሕዝባዊ ድርጅቶች ስለሚኖራቸው ነፃነቶች፣

1. የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች የምዝገባውን ሥነ-ሥርዓት እንዳጠናቀቁ ወዲያውኑ የሕግ ሰውነት ይኖራቸዋል ::

2. የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ዓላማቸውን ለማራመድ በዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች ሁሉ የመጠቀም ሙሉ መብት አላቸው ::

አንቀጽ 18

ስለሌሎች ሕጎች፣

1. ሌሎች ማናቸውም ሕጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ የፀኑ ይሆናሉ ::

2. በተለይም ሰብዓዊ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች /ለምሳሌ፣ የፍትሐ ብሔር ሕግ ከአንቀጽ 8 እስከ አንቀጽ 31፤ እንዲሁም የሠራተኛ የመብትና የግዴታ አዋጅ ውስጥ ያሉት ድንጋጌዎች/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩትን ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች የሚያሟሉ ይሆናሉ ::

## አንቀጽ ፲፱

ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች በተጨባጭ ወገንዱ ሥራ ላይ እንዲውሉ ስለሚያስፈልጉ ቅድ ቅድሚ ድጋፎች፤

የሰፊው ሕዝብ ወገን በዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች በተጨባጭ ሁኔታ ለመጠቀም እንዲችል ከመንግሥት ያለተቆጠበ ጥረት ይጠየቃል ::

ሀ/ የመንግሥት የመገናኛ የዜና ማሠራጫ መሣሪያዎች በሙሉ ለሕዝቡ አገልግሎት ክፍት ይሆናሉ :: የመንግሥት ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ ሬዲዮና ተሌቪዥን ለሕዝብ አስተያየቶች በቂ ያለ ቦታና ጊዜ ይመድባሉ ::

ለ/ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ አዳራሾች፣ የቲያትር ቤቶች፣ የሲኒማ ቤቶችና ማንኛውም ዓይነት ለሳ የመሰብሰቢያ ሥፍራዎች ለሕዝባዊ ስብሰባዎችና ውይይቶች ሰፋ ባለ መንገዱ በመድረክነት እንዲያገለግሉ ይደረጋል ::

ሐ/ ኢንዱስትሪዎች፣ ፋብሪካዎች ወይም ሌሳ የወዝ–አደር ክፖቶች ያለባቸው የማምረቻ፣ የማከፋፈያና የአገልግሎት ድርጅቶች ወዝ–አደሩ ለስብሰባና ለውይይት ወይም ትምህርት ሊገበይበት የሚችልበትን ቦታ ያዘጋጃሉ :: የጽሕፈትና የማባዣ መሣሪያዎችንም ለማቅረብ ያለተቆጠበ ጥረት ያደርጋል ::

መ/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ሌሎች የቢር ድርጅቶች ለትምህርት፣ ለውይይትና ለድርጅት አመቺ ሁኔታዎችን የመፍጠር ኃላፊነት አለባቸው :: ለምሣሌ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን በማዘጋጀት፣ በመሥሪያ ቤት የጽሕፈትና የማባዣ መሣሪያዎች የመጠቀም መብትና ዕድል እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ወዘተ... ::

## አንቀጽ ፳

ማስፈጸሚያ፤

1. ይህን አዋጅ የማስፈጸም ተግባርና ሥልጣን የጽሕፈት ቤቱ ነው ::
2. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በዚህ አዋጅ መንፈስ በመመርኮዝ ጽሕፈት ቤቱ ድንጋጌዎችን ሊያወጣ ይችላል ::

## አንቀጽ ፳፩

ቅጣት፤

ይህን አዋጅ የጣሰ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ::

## አንቀጽ ፳፪

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፤

ይህ አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችንን፣

የመሪውን ንቅናቄ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦር ለማድከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን በንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቀርበ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ በሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሄድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያስተማራቸውን ነፃነት በመገጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፣ከየትናጠም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መተስተሻ ሆነው በቆዩት በ<u>ታጠቅና</u> በ<u>ትግላችን</u> ስም መጠቀም ጀምረዋል:: የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም <u>ታጠቅና</u> <u>ትግላችን</u> በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው::እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያቃተውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወንጀገበር በመንዛት ለማፋፋም ነው::ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው:: ለማንኛውም፣የተለመደው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.DOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያነ፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች <u>ማህበር</u> አባልነትን የሚመለከቱ ጉን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንዲያስታውቁልን እንዲያስተላልፉልን እንጠይቃለን::ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው "ዓለም ዓቀፍ ፊዴሬሽን" በሚባል ስም የታወቀው የነ አሰፋወሰን - መገናኛ ሥም የወጣቶች ድርጅት ነው::

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በስኢተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ